በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!

(መጋረጃው ሲከፈት መልአከ ፅልመት በርናባስን እያዳፋ ይዞት ይወጣል በርናባስ ይቀበጣጥራል። አንዳንዴ በምድር ላይ ያሳለፈውን ሕይወት ይረገማል። አንዳንዴ ተስፋ ባለመቁረጥ መልአከ ፅልመትን ይለምነዋል)

በርናባስ (እንደ ማልቀስ እያለ) ውይ ውይ ውይ... አይ መከራዬ (3 ጊዜ) እህህህ... አይ ፍርጃ...ወዮልኝ...አይ ጉዴ... አረ ባክህ ቀስ በል! ምነው አንተን የበደለሁህ አስመሰልኸው

መ/ሞት መቀባጠሩን ትተህ ቀጥል። (ይገፈትረዋል)

በርናባስ (እያለከለከ) ኧረ ተው ትንሽ እንኳ ርህራሄ ይኑርህ... እሽ ለለምንህ ትንሽ ትንሽ ፋታ ስጠኝ

መ/ሞት ወድቆ መንፈራገጥ ጀርባ መምለጥ ነው! ቀጥል።

በርናባስ ወዮልኝ... አወይ ጉዴ... አይ እድሌ አይ እድሌ...

መ/ሞት የምን ዕድል ወዴት ወዴት ነው ነገሩ እድልህ ሳይሆን ስራህ ነው ለዚህ ያበቃህ

በርናባስ መብቃት አልከው አንተ ምን አለብህ አይ ጉዴ ገና የማያልቅ የመከራ ዘመን ይጠብቀኛል።

መ/ሞት ዝም በል (ያመናጭቀዋል)

በርናባስ ኧረረረ... (አቡነ ጴጥሮስን በመድረኩ ቀኝ ከርቀት ያያቸዋል) አባቴ ያድኑኝ አባቴ ስለ እግዚአብሔር ብለው ትንሽ፣ ትንሽ እንኳ ፋታ አገኝ ዘንድ ይርዱኝ

አቡነ ጴጥሮስ ቆዩ እስኪ ሁለታችሁም ተረጋጉ!

በርናባስ በፈጠረዎ አባቴ ትንሽ እርፍ አንድ እግዚአብሔርን ይለምኑልኝ

መ/ሞት (እየገተተ) ና ዝም ብለህ እረፍት ብሎ ነገር የለም።

በርናባስ ኧረ እባክዎን አባቴ እርስዎ እንኳ ይዘኑልኝ

አቡነ ጴጥሮስ ተረጋጋ የኔ ልጅ!

በርናባስ (ለመቅረት እየተጎተተ) መልአከ ሞት እንዴት እንደሚያንገላታኝ እያዩ እንዴት እረጋጋለሁ።

መ/ሞት አሁንም ትከሰኛለህ? የምትንገላታው እኮ በስራህ ውጤት ነው።

አቡነ ጴጥሮስ ምን አድርጎ ነው?

መ/ሞት ዕልፍ አራዊት እና እንስሳት የተፈጥሮ ሕግን አክብረው እየኖሩ የሰው ልጅ ግን ሰማያዊ መሆኑን ረስቶ በዘር በቀለም በቋንቋ ተባ‍ድኖ በወንዝ በድንበር እና በጎጥ ተከፋፍሎ ያለምንም ርህራሄ እርስ በርሱ ይገዳደላል። ምን ይሄ ብቻ በቤት ውስጥ እንኳን ሀሜት፣ ጥርጥር፣ ጥላቻ፣ ትዕቢት፣ ስስት፣ ራስ ወዳድነት እና ተንኮል ነግሧል።

አቡነ ጴጥሮስ ክርስቶስ ዘር ቀለም ቋንቋ ሳይለይ ኃጥእ ጻድቅ ሳይል በመስቀል ተሰቅሎ ከኃጢአት ባርነት ነፃ በማውጣት አንድ አደረገን እንጂ በውኑ ክርስቶስ ተከፍሏልን?

በርናባስ ኧረ በፍጹም እኔ እንደዚያ አላልኩም። ምን አልባት ሰይጣን አሳስቶኝ.....

መ/ሞት (ተናድዶ ያቋርጠዋል) ዝም በል! ከየትኛው መርሐ ግብሬ ላይ ተገኝተህ ነው ያሳሳትህህ? ምነዋ! አውደ ምሕረት ከማሞቅ እና ከማድመቅ ወጥተህ አባቶች ሲያስተምሩ ያልተሳሳትህ?

አቡነ ጴጥሮስ የኔ ልጅ በፍጹም እንዳትዋሽ!

በርናባስ እኔ'ኮ ለመዋሸት ፈልጌ አይደለም።

መ/ሞት አስመሳይ በአፉ እንጂ በልቡ ከፈጣሪው የራቀ ሕዝብ።

አቡነ ጴጥሮስ ልጄ! እግዚአብሔር ልብንና ኩላሊትን የሚመረምር በአንደበታችን የምንናገረውን ብቻ ሳይሆን በኅሊናችን የምናስበውን በውስጣዊ ብልቶቻችን የሚመላለሰውን ስሜታችንን ሳይቀር ያውቀዋል። ውሸት ደግሞ ኃጢአት ነው።

መ/ሞት (እየተፀየፈ) ኧረ ወደዚያ! በዓለም ላይ ከእንስሳ ያልተለየ የቆሸሸ ሕይወት እየመሩ ኋላም የማያልቅ የመከራ ዘመን ይጠብቃቸዋል።

በርናባስ አባቴ እኔ ቤተክርስቲያን እና ሀገሬ ከተደቀነባቸው ዘርፈ ብዙ ችግሮች የሚያወጣቸው ጥበበኛ ሰው ለማግኘት የምኳትን ሰው ነኝ።

አቡነ ጴጥሮስ ብሉይ እና ሐዲስን የተቀበሉ የአስተዳደር ጥበብን ለቀደምት እስራኤላውያን ያስተማሩ ሕዝቦች ዛሬ እንዴት ለራሳቸው መፍትሄ የሚፈልግ አንድ ሰው ታጣለህ?

በርናባስ አጣሁ!

መ/ሞት ወይ ማንነታችሁን ረስታችሁ ኢትዮጵያዊነት ተረት ተረት ሆኖባችኋል።

በርናባስ ኧረ አልተቀየረም! ደግሞስ ኢትዮጵያዊ መልኩን ወይስ ነብር ዥንጉርጉርነቱን ይለውጥ ዘንድ ይችላል?

መ/ሞት (በሹፈት) ድር ቢያብር አንበሳ ያስር! አንድነት ኃይል ነው! ከአንድ ብርቱ ሁለት መድኅኒቱ! ሁላችን በክርስቶስ እንተዋወቅ ብዙዎች ስንሆን አንድ ሥጋ የተባልነው ከሰማይ የወረደውን ያን አንዱን እንጀራ ስለምንካፈል ነው። ይህን ስናደርግ የአንድ አባት ልጆች መሆናችንን ያጎላልናል።.... አባባል እና ጥቅስ ብቻ! ተግባር ላይ ግን የላችሁም። አፋችሁ ለፈጣሪያችሁ ቅርብ ከልባችሁ ግን ሩቅ ነው።

አቡነ ጴጥሮስ መለያየት ከሰይጣን የሆነ የጨለማ ግብር ነው። ዘር፣ ቀለም፣ ቋንቋ፣ እውቀት እና ሀብት ለመከፋፈላችሁ ምክንያት ሳይሆኑ ያላችሁን አስተባብራችሁ ለሰማያዊ ቤታችሁ የሚሆን መልካም ፍሬ ለማፍራት ተጠርታችኋል። ስለዚህ በአንድነት በጸሎት ብትተሳሰቡ አምላካችን ፍቅራችሁን ተመልክቶ የመፍትሔ ሐሳብ ይጠቁማችኋል። ፍጹም ፍቅራችሁ ለዓለም ሁሉ ብርሃን ይሆናል። በዚህም የሰማይ አባታችን ይከብራል። ለመሆኑ የችግሮች ምንጭ ከየት ነው?

በርናባስ መነሻው ከውጭ ቢሆንም የውስጥ ችግርም አለ።

አቡነ ጴጥሮስ በክርስትና ሕይወታችሁ ዝላችኋል ማለት ነው?

በርናባስ ኧረ በፍጹም! እኛ እኮ በክርስቶስ ክርስቲያን ተብለን የተሰየምን፣ ከአብራከ መንፈስ ቅዱስ ከማህፀነ ዮርዳኖስ የተወለድን፣ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም የተገዛን፣ በፍቅሩ ገመድ የታሰርን፣ በሞቱ ሕይወትን ያገኘን በትንሣኤው ብርሃን የከበርን የእግዚአብሔር ልጆች ነን።

አቡነ ጴጥሮስ የክርስቶስ ፍቅር ከቶ ያልገባችሁ በክርስቶስ ክርስቲያን የሚለውን የተቀደሰ ስም በረከሰ ምግባር ለሌላ መሳቂያ መሳለቂያ አደረጋችሁት። በተሸከማችሁት እውቀት የምትመኩ ነገር ግን ተብትቦ ከያዛችሁ የክፋት ቋጠሮ አንዱን እንኳን መፍታት የማትችሉ አፈቀላጤዎች... ሰው ክቡር ሆኖ ሳለ ራሱን ሳያውቅ እንደሚጠፉ እንስሶች መሰለ።

በርናባስ ነጭ ነጠላ ለብሰን ያላደረግነው የለም፤ ኪዳን፣ ቅዳሴ፣ ሰርክ ጉባኤ፣ ገዳማት መሳለም ምኑ ቀርቶን።

መ/ሞት ነጭ ብትለብሱም ውስጣችሁ ግን ጠቁሯል። ንግግር እውቀት ነው። ተግባር ግን ፍሬ ነው። እግራችሁ በልማድ ተመላለሰ ጆሯችሁም ሰባ ልባችሁ ግን አልተሰበረም። ከዘረዘርካቸው ውስጥ ከመታደም ውጭ ትሳተፋለህ?

በርናባስ በትርፍ ጊዜዬ ከመሰል ጓደኞቼ ጋር በአገልግሎት እተጋለሁ።

መ/ሞት ምሥጢራትን ትካፈላላችሁ?

በርናባስ እሱ እንኳ ራሱን የቻለ ጊዜ የሚፈልግ ስለሆነ ብናስብበትም አላደረግነውም።

አቡነ ጴጥሮስ ለምን ትመላለሳላችሁ አትጸኑም፤ ትማራላችሁ አትለወጡም፤ ንስሐ ትገባላችሁ አትጸጸቱም፤ ታስቀድሳላችሁ አትቆርቡም። ክርስትና'ኮ የሚናገሩት ብቻ ሳይሆን የሚኖሩትም ጭምር ነው። የኔ ልጅ ያልኖራችሁበትን እምነት እና ዕድሜ መቁጠር እና መናገር ምን ዋጋ አለው? ለውጥን በስንፍና አናገኘውም የሚከፈለውን ዋጋ መክፈል አለብን።

በርናባስ እንግዲህ የንስሐ ዕድሜ እንዲሰጠን እየጸለይን ነው።

መ/ሞት (እየተናደደ) አንተ አሁንም ታሾፋለህ? ስንት ጊዜ የንስሐ ዕድሜ ተሰጣችሁ? ስንት ጊዜ ተማራችሁ? ስንት ጊዜ ተመከራችሁ? አንዱንም አልተጠቀማችሁበትም።

አቡነ ጴጥሮስ ያለ ተግባር ስብከት ብቻ ስለሆነ ልባቸው ደንድኗል።

በርናባስ የምንችለውን ያህል እንደ ጊዜው ለመኖር እየጣርን ነው። ለመሆኑ እርስዎ እንዴት ነው የኖሩት?

አቡነ ጴጥሮስ መሠረት ሳያውቅ ጣራ የሚንቅ ስለ አውሮፓ ግን ከክርስቶስ ልደት በፊት ጀምሮ ያለ ታሪካቸውን የሚሸመድድ ትውልድ።

በርናባስ ማለት?

አቡነ ጴጥሮስ እንዴት እንደኖርን እና ሀገራችንን እንዴት እንዳቆየናት ማወቅ አትፈልጉም፤ ደግሞም አታወቁም። ያኔ እናት ሀገር ኢትዮጵያዬን ቃሌን ተቀበይኝ ከገዳይሽ ተባብሬ ብከዳሽ ሰማይ እና መሬት ይክዱኝ። ብሞትም አጥንቴ እሾህ እና ስለት ሆኖ ጠላትሽን ይወጋዋል። ደሜም እንዳትከፋፈይ እንዳትቆረሽ መሬትሽን ይለስነዋል ብዬ እንኳን ሰው መሬቱም እንዳይገዛ አውግዤ ለሃይማኖቴ እና ለሀገሬ ራሴን አሳልፌ ሰጠሁ። ችግሩ እናንተ የተከፈለላችሁን ዋጋ አታውቁም። (በርናባስ በትካዜ ተመስጦ ይከታተላቸዋል) ምነው እመ ብርሃን በዘመነ ስደትሽ የረገጥሻትንና በአክብሮት በፍቅር የተስተናገድሽባትን ኢትዮጵያን በመከራ ናዳ ስር ወድቃ ስትቃትት ምሕረትን ከልጅሽ አልጠየቀሽላትም?

መ/ሞት አንተስ ለምን ዘመኑን ሳይቀር በስማቸው ያስጠሩ ልጆችን እንደወለዱ ወላጆች ለሀገሩ እና ለሃይማኖቱ ቀናኢ ልጅ አትወልድም?

በርናባስ (በመደነቅ ፈገግ እያለ) አይይ.. ምነው ጽድቁ ቀርቶ በቅጡ በኮነነኝ አሉ።

መ/ሞት እንዴት?

በርናባስ እንኳን ያን ያህል ጊዜ ልንታገስ ይቅርና ከዓመት ከሁለት ዓመት በኋላ ችግሩ የማን እንደሆነ እንኳ ሳናውቅ እንፋታለን።

አቡነ ጴጥሮስ በሃይማኖት ያልተደረገ ነገር ሁሉ ኃጢአት ነው።

መ/ሞት ላም ባልዋለበት... አሉ።

አቡነ ጴጥሮስ   እና ታዲያ ከበለሷ በምን ተሻልክ? ያልወለድከውን ጠቢብ የት ነው የምትፈልገው? የጻድቅ አባት እጅግ ደስ ይለዋል። ጠቢብንም ልጅ የወለደ ሐሴትን ያገኛል። ጠቢብ ልጅ አባቱን ደስ ያሰኛል። ሰነፍ ልጅ ግን እናቱን ይንቃል። የኔ ልጅ ማንም የቆመ ቢመስለው እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ። ያልተዘራ አይታጨድም።

መ/ሞት   ያለሽ መስሎሻል ተበልተሽ አልቀሻል ነው ነገሩ።

በርናባስ ያላችሁኝ በሙሉ ውስጤ ዘልቆ ተሰማኝ። ትእዛዛቱን የማልፈጽም ሕጉን የማልጠብቅ ወንጌልን ከመኖር ይልቅ መልሼ እንደ ገደል ማሚቶ የማስተጋባ ነኝ፤ እኔም ሆንኩ መሰሎቼ ፍሬ አልባዎች ከሆንን ይህ ጠቢብ ሰው እንዴት ሊገኝ ይችላል?

መ/ሞት   አንተ የምታውቀው ያየኸውን ነው። ነገር ግን ያላየሻቸው ወንጌልን በደንብ የሚኖሩ ጽኑዓን እኛ ቀና ብለን የማናያቸው አሉ። አንተ ያልቻልከው ጥበበኛ ልጅ መውለድ ብቻ ሳይሆን ማየትም ጭምር ነው።

በርናባስ   አለመኖሩ እንጅ ካለ እንዴት ማየት አልቻልኩም?

መ/ሞት   ራስህን ሳታስተካክል እንዴት ትችላለህ?

አቡነ ጴጥሮስ   ዘረኝነት፣ መከፋፈል፣ ስስት፣ ቂም በቀል በእጅህ አለ። ፍቅር ግን የለህምና ማየት አትችልም።

በርናባስ   ልክ ናችሁ ንሴብሆ ባልኩበት አንደበቴ ና በለው፣ አሼሼ ገዳሜ እላለሁ። ምን ዋጋ አለኝ አባቶቻችን ምግባችንንና ልብሳችንን ካገኘን ይበቃናል አሉ። እኔ ግን በቃኝን አላውቃትም። ለሥጋዬ ምቾትን ፍለጋ አብዝቼ እባክናለሁ።

አቡነ ጴጥሮስ 'በነፃነት ልንኖር ክርስቶስ ነፃ አወጣን፤ እንግዲህ ጸንታችሁ ቁሙ እንደገናም በባርነት ቀንበር አትያ' የሚለውን የመንፈስ ቅዱስ ማስጠንቀቂያ ችላ አትበል። ክርስቶስ ከፈጠረው መንጋ ቡድን ወደፈጠረው መንጋ አትሂድ። በጎ ስራን አጽንቶ ከያዙት እግዚአብሔርን ያስገኛል። ሰይጣን የሚንቀው በጎ ሥራ የለምና የጀመራችሁትን በጎ ሥራ አጽንታችሁ ያዙ። የኔ ልጅ የቤተክርስቲያንን ችግር ሳላውቅ ቀርቼ አይደለም። በለምለሙ መስክ ተኩላዎች እና አስመሳዮች በዝተው መንጋው እየታመሰ ነው። አንተም እግዚአብሔርን ያገለገልሁ እየመሰለህ እንዲሁ በስሜት ብቻ እየሮጥህ ያሳለፍከው ጊዜ ይብቃህ። እግዚአብሔርን በመፍራት በማስተዋልና በጥበብ ሆነህ ወደ አገልግሎት ተመለስ። ለተፀፀተ ልብ ደግሞ አይደለም አንድ ቀን አንድ ሰዓት ይበቃዋል። ከዚህ በኋላም እስከ ሞት ድረስ የታመንህ ሁን የጽድቅንም አክሊል ታገኛለህ።

መ/ሞት መቼስ ችግሩን የሚፈታው አንድ ሰው ብቻ አይደለም መፍትሔውን ከያዙት ሰዎች መካከል አንዱ አንተ ነህ። ሌት እና ቀን እየደከሙ ለውጡን በተስፋ የሚጠብቁ አሉና አንተም የተግባር ሰው በመሆን ወደ ምድር ሂድና እነሱን ተቀላቀል ልልህ አልችልም።

በርናባስ   አይሆንም። አሁን ራሴን ማዳን አለብኝ።

መ/ሞት   ኦርቶዶክሳዊነት ተደጋግፎ ማለፍ ነው እንጂ ጥሎ ማለፍ አይደለም። ብርቱው ብቻ ይኖራል የሚል የዳርዊን የክህደት አስተምሮ ነው ትላላችሁ። በተግባር ሲሆን ራሴን ማዳን አለብኝ። አሁን ጊዜዬን በከንቱ ማባከን አልፈልግም ና ቀጥል። (እጁን ሂዶ ይይዘዋል)

በርናባስ   ወንጌልን መኖር አለመኖር ነው የሚለውን እኔን ጨምሮ ሁሉም ሰው ያውቃል።

አቡነ ጴጥሮስ   በእናንተ ሰበብ የእግዚአብሔር ስም በአሕዛብ መካከል መሰደብ የለበትም። ልጄ ክርስትና የሌላውን ሸክም መሸከም ነው። አንዱ ለአንዱ ራሱን አሳልፎ እንዲሰጥ ክርስትናችን አያዘዘችን ክርስቶስ አርአያ ሆኖን አባቶችም በኑሮ

አሳይተውን ሳለ ቅድሚያ እኔ ለ'ኔ በሚል ራስ ወዳድነት እና ብልጣብልጥነት መጓዝ ኦርቶዶክሳዊ ጠባይ አይደለም። ዓለም በክርስቲያኖች የተቀደሰች አኗኗር ትፈወሳለች። (ትተዉት ይወጣሉ)

በርናባስ እና ጥለውኝ ሊሄዱ ነው! እባክዎ ትተውኝ አይሂዱ እባክዎ... አባክዎ...(መ/ፅልመት ትንሽ ይጎትተውና ለቶት ይወጣል። ሲለቀው ተንደርድሮ ወንበር ላይ ይቀመጥና ፊቱን በእጁ ሸፍኖ) በፍጹም... በፍጹም አልሄድም....

ስምረት (ከመኝታ ክፍሏ እየተጨናበሰች እና እየተርበተበተች ወጥታ) በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ...(ደጋግማ ታማትባለች) ምንድነው የተፈጠረው?....ወይኔ አምላኬ?....በርና ምንድነው የሆንከው?

በርናባስ   አልሄድም ተወኝ!

ስምረት   የት?

በርናባስ   እዚያ የስቃይ ቦታ አትውሰደኝ ተወኝ

ስምረት   እንዴ በርናባስ ምን ምን ሆነሃል?...ወላዲተ አምላክ! ብቻህን እኮ ነው ያለኸው

በርናባስ   ተወኝ (እየተነሣ) አልሄድም ብያለሁ አ...ል...ሄ...ድ ም። (ሲያያት ባለቤቱ ናት) እንዴ የት ሄደ?

ስምረት   (ታማትባለች) ማን?

በርናባስ (ባለማመን እየተርበተበተ) ደ...ደ...ደስ...ደስ ይላል። (በፈገግታ) ለካ እኔ ነኝ የመጣሁ።

ስምረት ስንተኛ'ኮ ጤነኛ ነበርህ። በሌሊቱ አስነሥቶ የሚያስለፈልፍህ ምንድነው? ለምን አትናገርም? እኔንም በጣም እያስጨነቅኸኝ ነው ምን ሆነሃል?

በርናባስ   (ከዝምታ በኋላ ለማልቀስ እየቃጣው) ተመስገን አምላኬ ሞቼስ ቢሆን ይሄኔ ሲኦል ውስጥ ነበርኩ አይደል?

ስምረት ምንድነው? የሆንከውን አትናገርም እንዴ!?

በርናባስ ዳዊት እና ነጠላዬን አቀብይኝ አንቺም ቶሎ ለባብሰሽ ውጪ ወደ ቤተክርስቲያን እንሂድና አባን ከኪዳን እንደወጡ እናግኛቸው።

ስምረት እንዴ! የሆንከውን ሳትነግረኝ?

በርናባስ ምንም ጊዜ ሳናባክን መፍጠን አለብን። ለረጅም ጊዜ ስንመኘው እና በጉጉት ስንጠብቅ የነበረው የንስሐ ዕድሜ አሁን መሆኑን አወቅሁ። ለሁሉም ነገር አባታችንን እናግኛቸው። ፍጠኚ።

ስምረት እሺ መጣሁ ጠብቀኝ። ግን...? (ልታመጣ ትገባለች)

በርናባስ ስምረት ሌላውን አየሄድን እነግርሻለሁ።(በረጅሙ ይተነፍሳል) እፉፉፉ....ተመስገን። በቸርነቱ ብዛት ቢታገሰኝ ያልበደልሁ መሰለኝ። ከዚህ በኋላ እንደፈቃዱ እና እንደረዳን መጠን ወደፊት እንጂ ወደኋላ መመለስ የለም።

ስምረት በዚህ ሰዓት አስነሥቶ እንደዚህ እስከሚያደርግህ የደበቅኸኝ ምን ቢገጥምህ ነው? በትዳር ላይ የግል ጉዳይ ምናምን የሚባል ነገር አይሠራም።

በርናባስ   እሺ ግን እየሄድን። (ወደ ቤተክርስቲያን ለመሄድ ይወጣሉ)

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

አሸናፊ ቢሻው ሐምሌ **2011** ዓ.ም